# የአሸቸኳይ ግዜ አዋጁ መፅደቅና እንድምታው

ሁላችንም እንደምናውቀው ከሁለት ሳምንት በፊት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የአሸኳይ ግዜ አዋጅ በማወጅ በህገ- መንግስቱ አንቀፅ 93 ተራ ቁጥር 2(ለ) መሰረት በ15 ቀናት ውስጥ ለህዝብ ተወከዮች ቀርቦ እንደሚፀድቅ ግልፅ ተደርጎ ተግባራዊ መሆን ጀምሯል:: ይህን ተከትሎ በተለያዩ የህብረት ሰብ ክፍሎች የተለያዩ ሃሳቦች ሲነሱ ቆይተዋል:: በአንድ በኩል አሸቸኳይ ግዜ አዋጁ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ እንዲያውም ባለፈው ግዜ መነሳት አልነበረበትም የሚል የአብዛኛው የአገራችን ሰላምና ልማት ፈላጊ ህብረተሰብ የሚያነሳው ሲሆን የተወሰኑ ከግርግሩ ተጠቃሚዎች (የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል እንደሚባለው) በተለይ ደግሞ ውጭ አገር ተቀምጠው እዚህ ምስኪኑና ስራ ያልተፈጠረለት ወጣት በሞተው እነሱ ስልጣን በአቋራጭ ለመያዝ የሚቋምጡት የትምክህትና የጥበት ኃይሎች ከግብፅና ከሻዕቢያ በሚወረወርላቸው ርፍራፊ ብጥብጡን እንዲቀጥል ስለሚፈልጉ የህዝብ ተወካይ አባላት በግልም እያገኙ ወደስብሰባው እንዳይገቡ ከገቡም እንዲቃወሙ አበክረው ሰርተዋል:: አንዳንድ ከፍተኛ ባለስልጣናት (የወደ ፊቱ ጠቅላይ ሚኒስተር ለመሆን ቅስቀሳ የጀመሩት ሳይቀር) የዚህ ሰለባ በመሆን በተጠራው ስብሰባ ሳይገኙ ቀርተዋል::

ግን እንደ ታላቁ ሰውና ከፍተኛ ምሁር ለዚች አገር ችግር መፍትሄ ነኝ ብለው የሚያስቡና እንዲወራላቸው ያደረጉት ብቃት ያላቸው ዶ/ር አብይ በተጠራው የህዝብ ተወካዮች ስብሰባ ለምን ቀሩ? በዚች አገር ከብጥብጥ ሰላም፣ ከውድመት ልማት፣ ወደኋላ ከመጎተት በህዳሴ ጉዞ ወደፊት መውሰድ ከሚፈልግ ሰው አሁን አገራችን ለገጠማት ችግር ወደመፍትሄ ይወስዳታል አይ አይወስዳትም ተብሎ ለመወሰን ከተጠራው ስብሰባ ገብተው አንዱን አቋም ይዘው ለማሳመንና ለማስወሰን ዝግጁ ካልሆኑ የቱ ላይ ነው ብቃታቸውና ለዚች አገር ይታደጋሉ የሚያስብላቸው:: እንደኔ ከሆነ በየፌስ ቡኩና ሚድያው እየተሰራጨ ያለው ወሬ ትክክል ሳይሆን አይቀርም:: እሱም አቶ ጃዋር የተባለው የግብፅና የኢሳያስ ተላላኪና ምላስ እንጂ ፈጣሪ ጭንቅላት ያልፈጠረበት አለቃቸው እንዳትሳተፍ ስላላቸው ነው እንጂ ከዚህ የሚበልጥ አንገብጋቢ ስራ አልነበራቸውም ይባላል:: ለነገሩ ምን ያድርጉ ዶ/ሩ ቤተሰቦቻቸው በሙሉ አመሪካን አገር ካሻገሩ ቆዩ እዚህ ብቻቸው ናቸው ያሉት እናም ቤተሰቦቻቸው በአቶ ጃዋር ቁጥጥር ስር ናቸው ምን ይታወቃል እሳቸው ከኢንሳ ይዘዋት በወጡት ትንሽ እውቀት ተመክተው ስንት የኦህዴድ አመራር አስፈራርተው የለ:: አቶ ጃዋርም ቤተሰቦችህ እኔ ጋር ናቸው ብሎ አስፈራርተዋቸው ሊሆን ይችላል:: ወይም ደግሞ እንደሚባለው እሳቸው አዋጁ ስለማይፈልጉትና እንዳይፀድቅም ምክርቤቱ ማሳመን ስለማይችሉ አቅማቸው እንዳይጋለጥም ሰግተው ሊሆን ይችላል:: ያም ሆነ ይህ በአንድ ወቅት ታላቁ መሪ ክቡር አቶ መለስ እንዳሉት ለማንኛውም ሰው የአገራችን ህዝቦች እንጂ ምንም አይነት አቅም ይኑራቸው የውጭ ሃይሎች መድን ሊሆኑዋቸው አይችሉም::

እዚህ ላይ የተከበሩ አቶ አባዱላን ሳላመስግናቸው አላልፍም ምክንያቱም ትንሽም ብትሆን የቀረቻቸውን ልማታዊና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ (በወላፈኑ ያለፉና ያለፈውን የከረፋ ስርአት ስለሚያቁት) ተጠቅመው አሁን ያላቸው የሰላም ፍላጎት ያሳዩበትና የእነ ዶ/ር አብዪ ከለላ መሆን ለማቋረጥ የወሰኑበት ሂደት በመሆኑ ይህ ነጌ የኦሮሞ ህዝብ ሰላም አግኝቶ በመስራት ከልማቱና እድገቱ ተጠቃሚና ከሌሎች

የአገራችን ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ትክክለኛ በፍላጎትና በመተማመን አድነቱ ሲያጠናክር ውለታዎ አይረሳውም የተቀሩት የአገራችን ህዝቦችም እንደሚወድዎት አልጠራጠርም በአንፃሩ በጠባቦችና ህገ-ወጦች እንደማይወደድና በየሚድያው ዱላ እንደሚወርድዎት (ተጀምረዋል) የሚስቱት አይመስለኝም

ወደተነሳሁበት አብይ ጉዳይ ልግባና የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት ስብሰባ ከመካሄዱ በፊት ሲቀሰቀስ የነበረውና ሲተላለፍ የነበረው መልእክት ለተመለከተው ሰው እውነትም እነዚህ ሰዎች እንመራታለን የሚሉዋት ሀገር ያላት ህገ-መንግስትና የደረሰችው ደረጃ ምንም እውቀትና ግንዛቤ እንደሌላቸው ነው የሚያሳየው:: ሲተላለፍ ከነበረው በርካታ መልእክት አንዱን ብቻ ብናያት ህገ-መንግስቱ ለዚህች አገር ህዝቦች የሚሰጠው ዋስትና በጣም አስተማማኝ መሆኑን መገንዘብ እንችላለን::

የኦሮሞ ክልል ከሁሉም ክልሎች በላይ ብዙ የህዝብ ቁጥር ያለው ስለሆነ በተወካዮች ምክርቤት ያላችሁ ተወካይ ባትሳተፉ ወይም ቦይኮት ብታደርጉ ወይም ደግሞ ብትቃወሙ አዋጁ አይፀድቅም የሚል መልእክት ነበር ሲተላለፍ የነበረው::

ይህ የህዝብ ቁጥር ከሃያ ሰባት አመት በፊት ጀምሮ በተደጋጋሚ በአንዳንድ ምሁራን ተብየ ስልጣን በአቅምና በችሎታ ሳይሆን በብሄር ተሸፍኖ ሲነገር ይሰማል፤ የኦሮሞ ህዝብ ቁጥር ከሁሉም የሚበልጥ ስለሆነ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ቦታ መሰጠት አለበት፤ የኦሮሞ ህዝብ ቁጥር ብዙ ስለሆነ ቋንቋው የፌደራል የስራ ቋንቋ መሆን አለበት፤ የኦሮሞ ህዝብ ቁጥሩ ብዙ ስለሆነ አዋጅ ሊሽር ይችላል የሚሉ ሌሎችም ሲነሱ ይስተዋላል:: እነዚህ አስተሳሰቦች ከአሁን በፊት በብዛት ሲነሱ የነበሩት በተወሰኑ በውጭ የሚገኙ እንደ ኦነግ የመሳሰሉ ጠባቦችና በውስጥ ደግሞ እንደነዶክተር መራራ የመሰሉ በስልጣን ፍላጎት እንጂ አቅም የሌላቸው ለኦሮሞ አንድም የረባ ስራ ያልሰሩለት ከመጣ መንግስት ሲሞዳሞዱ እድሜአቸው የጨረሱ ሰዎች ነበር:: አሁን አሁን ደግሞ ለህዝብ ልኡላዊነትና የስልጣን ባለቤትነት የታገለው አሁን ላለው ተአምራዊ ለውጥ ከሌሎች ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች በግንባር ቀደምትነት ከታገለውና ለውጥም ካመጣ ድርጅት (ኦህዴድ) በስልጣን ላይ ካሉ በጠባብ አመለካከታቸውና ለስልጣን ካላቸው ጉጉት የተነሳ ድርጅቱን ጠልፈው የጥያቄው አቀኝቃኝ ሆነው ብቅ ብለዋል::

የኦሮሞ ህዝብም ለዘመናት አብሮ ከኖራቸው ወንድምና እህት ከሆነው የተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ሊነጥሉት አበክረው መስራት ጀምረዋል:: ደግነቱ እነዚህ ጥያቄዎችና አስተሳሰቦች የኦሮሞ ሰፊው ህዝብ አጀንዳና አስተሳሰብ አይደሉም የሰፊው የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ የመልካም አስተዳደርና የፍትህ፤ የስራና እንጀራ፤ ከተገኘው እድገት የተጠቃሚነት ጥያቄዎች እንጂ እኔ ብዙ ቁጥር ስላለኝ ሁሉም እኔ ልቆጣጠር አላለም ይህ ከኦሮሞ ህዝብ ባህልና እሴት ከገዳ ስርአት ባለቤትነቱና ዲሞክራሲያዊ የስልጣን ሽግግር ባህል ያፈነገጠ አካሄድ በተአምር የሚቀበለውና የሚያስበው አይደለም:: ግን ምን ያደርጋል ጠባቦችና ጥምክህተኞች ቆመንልሃል ለሚሉት ህዝብ ነው ቅድሚያ ሰለባ የሚያደርጉትና አሁንም እየሆነ ያለው ይኸው ነው::

የጠባቦች ፍላጎት ፍላጎትና ምኞት አሁንም ከተቻለ እነሱ የበላይ የሚሆንባት ኢትዮጵያ መፍጠር ካልሆነላቸው ደግሞ የኛ የሚሉት ብሄር በመገንጠል እነሱ የበላይ መሆን የሚል ሁለት አማራጭ ይዘው

ነው የሚንቀሳቀሱት ከትምክህተኞች የሚለያቸውም ይህ ነው በአሁኑ ግዜ ሶስተኛ የተጨመረ ይመስላል ሁለቱም ካልተሳኩ ፈርጥጦ መጥፋት (አገር ጥሎ እንደ ጃዋር መጥፋት):: አሁንም የኦህዴድ አዲሶቹ ባለስልጣናት ይህን ተግባራዊ የሚሆንበት መንገድ ነው እየተጓዙ ያሉት:: በአንድ በኩል ኢትዮጵያዊነት ሱስ ነው ለኢትዮጵያ አንድነት እንታገላለን እያሉ ሲሰብኩ ይታያሉ (የሚሉት በቅጡ እንደማያውቁት ግልፅ ቢሆንም) በሌላ በኩል ደግሞ የጠቅላይ ሚኒስትር ቦታ ካልተሰጠንና ኦሮምኛ የፌደራል የስራ ቋንቋ ካልሆነ ሞተን እንገኛለን እያሉን ነው ለዛውም ከድርጅታቸው ባህልና አሰራር ወጣ ባለ መንገድ:: በሶስተኛው አማራጭ ምናልባት ሁለቱም ካልተሳኩ ቤተሰብህን ከአገር በማስወጣት ለመኮብለል ማመቻቸት::

ይህ ቅጥ ያጣ አካሄዳቸው ነው ግርግሩና ብጥብጡም የፈጠረው:: መንግስት የብጥብጡ መነሻ የራሴ ድክመቶች ባለማረሜና እድገቱን የሚመጥን አመራር ባለመስጠቴ ነው በማለቱ ለነሱ እንደማይመለከት በመቁጠር ከደሙ ንፁህ ነን ለማለትም ይከጅላቸዋል:: ለዚህ ተጨባጭ ማሳያው በአንድ ወቅት የአራቱ ድርጅቶች ሊቃነመናብርት በተሌቪዠን መስኮት ብቅ ብለው ባስተላለፉት መልእክት አቶ ለማ መገርሳ የተናገሩት ልብ ይለዋል:: በወቅቱ አቶ ለማ ያሉት ይህ ሁሉ ችግር በህወሓት ውስጥ የተፈጠረው ቡድን እኛ ጋርም ደርሶና በአንዳንድ ጥገኛ አስተሳሰብና ተግባር ያላቸው የትግራይ ተወላጆች የፈጠሩት ነው ብለውናል ድንቄም ከደሙ ንፅህነት:: እርግጥ ነው በህወሓት ውስጥ ችግር ነበረ በዚህ ችግር ግን ከሁሉም በላይ የተጎዳው የትግራይ ህዝብ ነው ከዛ ውጪ ህወሓት በኢህአደግ ውስጥ ባለው ተሳትፎ በአገር ደረጃ ለተፈጠር ችግርም ተጠያቂ ነው:: በሌላ በኩል አንዳንድ ጥገኛ የትግራይ ተወላጆች የኦሮሞ ተወላጆች ከኦሮሞ ህዝብ ቁጥር ሊጫወቱና ቁማር ለመጫወት እንደሚፈልጉ የትግራይ ህዝብ ለዚህች አገር እድገትና ዲሞክራሲያዊ አንድነት ሲባል የከፈለው ትርፍ (ከሁሉም የበለጠ) መስዋእትነት በማጉላት ቁማር መጫወት የሚፈልጉና የሰሩ የሉም ባይባልም ጥገኛ አመለካከት በሁሉም አለ ስለሆነም እገሌ እገሌ ሳይባባል በጋራ ለዚህ ፀረ ህዝብ አመለካከትና ተግባር መታገል ነበር የሚያዋጣው ጣት ከመቀሰር:: ካልሆነ አንድ ጣት በቀሰርክ ቁጥር አራቱ ጣቶች ይቀሰሩብሃል የሚባለው አባባል ነው የሚመጣው::

እነዚ ከላይ ለመጥቀስ የሞከርኳቸው ከቅርብ ግዜ ወዲህ እየተስፋፉ ያሉት ፀረ-ህዝብ አመለካከቶችና ተግባራት ናቸው እንግዲህ አገራችን የጀመረችውን የህዳሴ ጉዞ እንዲደናቃቀፍና መንግስት ተረጋግቶ በመደበኛ አደረጃጀቱና መዋቅሩ መስራት እንዳይችል ያደረጉት በመሆኑም መሰረታዊ መፍትሄው እነዚህ ችግሮች ከመሰረታቸው በሰከነ መንገድ መፍታት (የኢህአደግና የመንግስት የቤት ስራ) ቢሆንም ይህን ለማድረግ ግን ያለውን የፀጥታ መደፍረስ ማረጋጋት ያስፈልጋል ስለሆነም አሸቸኳይ ግዜ አዋጁ በራሱ ግብ ሊሆን አይችልም ይልቁንስ

1. መንግስት ከላይ እስከታች የተዘረጋው መዋቅር መደበኛ ህዝብን የማገልገል ስራው በአግባቡ እንዲያከናውንና የሚነሱ የህዝብ ጥያቄዎች ለመለየት የሚያስችለው ግዜ እንዲያገኝ
2. ህዝቡ ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ ህገ-መንግስታዊ መብቱ ተግባራዊ የሚያደርግበትና ተረጋግቶ ጥያቄዎቹን በማቅረብ የመፍትሄው አካል የሚሆንበት እድል ለማመቻቸት

3. የተጠለፉት የህዝብ ጥያቄዎች ከህገ-ወጦችና የቀለም አብዮተኞች እጅ በመንጠቅ ትክክለኛ ባለቤት እንዲኖራቸው ለማድረግ
4. ህገ-ወጦችና አገሪቱ ለማፍረስ የተነሱት የቀለም አብዮተኞች ለማጋለጥ
5. መጨረሻም አገሪቱ ወደ መደበኛ እንቅስቃሴዋና የህዳሴ ጉዞ ስራዎችዋን ለመመለስ የሚጠቅም አዋጅ ነው:: እነዚህ ወጤቶች ደግሞ መንግስት በመደበኛ መዋቅሩ ተጠቅሞ ሊከውናቸው ያልቻለበት ሁኔታ በመፈጠሩ ነው አዋጁ ያስፈለገው::

እነዚህ ጥቅሞች ብቻ ሳይሆኑ ለመላው የአገራችን ብሄር ብሄረሰብና ህዝቦች ዋስትናም ናቸው:: እነዚህ ዋስትና የማይሆኑት ለቀለም አብዮተኞችና ለህገ-ወጦች ብቻ ነው ስለሆነም በህዝብ ተወካዮች ስብሰባ ግዜ የተነሳው ጥያቄ ከዚህ አንፃር ውሃ የሚቋጥር አይደልም ሊበሏት የፈለጉ……ካልሆነ::

የአዋጁ መፅደቅ ይህን ያህል የሚጠቅም እያለ ግን የህዝብ ብዛታችን ተጠቅመን እንዳይፀድቅ እናደርጋለን ሲፀድቅም በዚህ ህግ አንገዛም እየተባለ ነው ድሮውም ህጉ ያስፈለገው እንደእናንተ አይነቱ ለሆዱ ያደረና ህግን የማያውቅ ለመለየት ነው የወጣውና ችግር የለውም እላለሁኝ:: በነገራችን ላይ እነዚህ ሰዎች በአብዝሃ ህዝብ የተደገፈ ህግ የማይገዙ ከሆነ በየትኛው ህግ ነው አገር ለማስተዳደር ቅስቀሳ እያደረጉ ያሉት?

በመጨረሻ እነዚህ ሰዎች በህዝብ ብዛትና በህገ-መንግስቱ መካከል ያለው አንድነት እንዴት ነው የሚተረጉሙት? ህገ-መንግስቱ እኮ በዚህች አገር ያሉት ብዙ ቁጥር ይኑራቸው ትንሽ እኩል መብት የሰጠና በእኩልነት ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንጂ ብዙ ቁጥር ያለው ብሄር (ክልል) የበለጠ ተጠቃሚና ፈላጭ ቆራጭ እንዲሆን ትንሽ ቁጥር ያለው ደግሞ ፈፃሚና ተመልካች እንዲሆን ተደርጎ አልተቀረፀም:: ሁሉም ብሄር ብሄረሰብና ህዝቦች እኩል እንደህዝብ ብዛታቸው ተሳታፊና ወሳኝ እንዲሆኑ፤በሚወሰኑ ውሳኔዎችም እኩል ድምፅ እንዲኖራቸው፤ ምናልባት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚያዘው ወንበር በህዝብ ቁጥር ስለሆነ ማንነታቸው የሚመለከቱ ውሳኔዎች በፌደረሽን ምክርቤት እንዲሆኑ ሲደረግ እነዚህ አይነት ፀረ-ህዝብና ህዝበኛ አመለካከቶች እንዳይከሰቱ ነበር::

በቁጥር እንጫወት ከተባለም የኦሮሞ ብሄር ህዝብ በተናጠል ከእያንዳንዱ ብሄር ህዝብ ይበዛል እንጂ በድምር ከሁሉም ክልሎች (ብሄሮች) ቁጥር $^{1}/_{3}$ኛም እኮ አይሆንም እንዴት አይነት ጨዋታ ነው:: ስለሆነም እባካችሁ ይህ ትላንትና በትምክህተኞች ስቃዩን ያየ ህዝብ አሁን ደግሞ በሰራችሁት ጥፋት ላለመጠየቅ ስትሉ በጠባብ ፍላጎታችሁ እንዲሰቃይና ከሌላው ተፈ,ቃቅሮና ወዳጅ ሆኖ ተጋብቶ ተዋልዶ ለዘመናት የቆየው ህዝብ እንዲነጥልና እንዲጠላ አታድርጉት::

ቸር እንሰንብት

ካሕሳይ ቃሉ
የካቲት 24/2010